# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 340 ህዳር 5 2007 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ወያኔ ታጋዮችን ቢያስር ትግሉን አያስርም። በእጦት ኑሮዓችን በማመሰቃቀል በድህነት ሊያንበረክከን ቢሻም፣ በፍጹም አንበረከክለትም። በተዘረፈ የድሆች ድካም ህንፃዎችን ቢገነቡም የራስ ባልሆነ ጌጥ አንኮራም። የወያኔ የሆነ የኛ አይደለም፤ የእነሱ መከበር የኛ መከበር አይደለም። ወያኔ እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ገዢና ተገዢ፤ በዳይና ተበዳይ፣ ገፊና ተገፊ ናቸው።

ተበዳይና ተገፊ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘረኞች፣ ሙሰኞችና ከፋፋዮች የህወሓት ባለሥልጣኖቻቸውና ሎሌዎቻቸው ላይ ይነሳሉ።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ከ40 በላይ በምእራብ አርማጭሆ ተወላጆችና ታጣቂዎች ወያኔን ለመፋለም በርሃ ገቡ

ከሰሞኑ በምዕራብ አርማጭሆ በግፈኛው የወያኔ አገዛዝ የተማረሩ ከ40 በላይ የአካባቢው ተወላጆችና ታጣቂዎች ከነፃነት ሃይሎች ጋር በመሆን አገዛዙን ለመፋለም በመወሰን በርሃ መከተታቸውን የአካባቢው ዘጋቢያችን ያደረሰን መረጃ ያመለክታል። እንደ ዘጋቢያችን መረጃ ግለሰቦቹ በርሃ ለመከተታቸው አብይ ምክንያ ከሰሞኑ የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በአብርሃ ጅርሃ ከተማ የተቀሰቀሰውን ሕዝባዊ ተቃውሞ ተከትሎ፥ አገዛዙ ሕዝባዊ ተቃውሞውን ለማፈን ተሰሚነት አላቸው በሚላቸው ግለሰቦች እንዲሁም በምእራብ ዓርማጭሆ በሚገኙ የተቃዋሚ ድርጅት አመራሮችና አባላት ላይ እያደረሰ ባለው ከፍተኛ ወከባ በመቆጣታቸው እንደሆነ ታውቋል። ግለሰቦቹ አገዛዙ በአካባቢው እያደረሰ ባለው መጠነ ሰፊ ሕዝባዊ በደሎች በተለይም ከሱዳን ጠረፍ ጋር ተያይዞ ፋሽስታዊው አገዛዝ በአርማጭሆ ተወላጆች ላይ የሚደርሰውን የግፍ ግድያ እና ዓፈና እንዲሁም አገዛዙ በአጠቃላይ በአገሪቱ ላይ አጠናክሮ በመውሰድ ላይ ያለውን የከፋ አፈናና እስራት በግንባር ቀደምትነት ይቃወሙ እንደነበር ተነግሯል።

የአካባቢው ተወላጆችንና ታጣቂዎችን በማስተባበር በረሃ ይዞ የከተተው አቶ አበበ ካሴ የተባለ ግለሰብ መሆኑ የታወቀ ሲሆን ግለሰቡ በአካባቢው የታወቀና ዝነኛ የባህል ዘፈን አቀንቃኝ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። ተወዳጁ የባህል ሙዚቃ አቀንቃኝ አበበ ካሴ በፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ሹማምንት አማካኝነት ለሱዳን በተሰጠው ለም የጠረፍ መሬት በሞቆርቆር፤ ግንባር-ቀደም ሆነው በሚናገሩ የምእራብ አርማጭሆ ገበሬዎች ላይ አገዛዙ የሚፈጸመውን ድብቅ ወንጀል በማጋለጥና በማውገዝ፥ እንዲሁም በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ ከፍተኛ ከበሬታና ተወዳጅነት የነበራቸውን የአገር ሽማግሌ ባሻ ጥጋቡ ሚስጥራዊ ሞት ዙሪያና፥ በቅርበት የሚያውቀውን በአገዛዙ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ሙሰኝነትና ጥቅማ ጥቅም መከላከያ ሰራዊቱን ለሁለት እየከፈለዉ መሆኑ ተሰማ

በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ በፖለቲካ እና በጥቅማ ጥቅም ጉዳዮች ዙሪያ የተጀመረው ከፍተኛ አለመግባባት ተከትሎ የሰሜን፤ የደቡብ፤ የምስራቅ እና የምእራብ እንዲሁም የማእከላዊ እዝ ውስጥ ያሉትን እና በሰራዊት ውስጥ ሽብር ይነዛሉ፤ ጥያቄ ያነሳሉ የተባሉ ጄኔራሎች፤ እንዲሁም ከሙቶ አለቅነት እስከ ኮሎኔል ማእረግ ያላቸው መኮንኖችን የምደባ ቦታቸውን በመቀያየር እና በሕወሓት ቅጥረኛ ወታደራዊ የደህንነት ሰዎች መካከል በመከተት ምንም አይነት እንቅስቃሴ እንዳያድርጉ ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ ከበላይ የህወሃት ቱባ የጦር ሹማምንቶች ተዘጋጅቶ መውረዱን የውስጥ ምንጫችን ያደረሰን መረጃ አመልክቷል። በመከላከያ ሰራዊቱ መካከል የተጀመረው አለመግባባት በከፍተኛ ሁኔታ ስር መስደዱን ያደረሰን ምንጫችን ምናልባትም ለችግሩ እልባት በቀላሉ ሊበጅለት እንደማይችል የተረዱት የአገዛዙ ቅጥረኛ የጦር ሹማምንት ሃይል የተቀላቀለበት እርምጃ ለመውሰድ ሊነሱ እንደሚችሉና ይህም ችግሩን የበለጠ ሊያወሳስበውና በሰራዊቱ መካከልም ግጭትን ሊያስከትል እንደሚችል አመልክቷል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከዚህ ቀደምም በተመሳሳይ መልኩ የህውሃት ቅጥረኛ የጦር ሹማምንት ከሰራዊቱ ለተነሱ በርካታ የፓለቲካና ጥቅማ ጥቅም ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት በመቸገራቸው በሰራዊት አባላት የተለያዩ ጫናዎችን ለማሳደር ቢሞክሩም ለችግሩ እልባት ሊያመጡ አለመቻላቸው የሚታወስ ሲሆን በተለይ አሁን ላይ እጅግ እየተባባሰ የመጣውና ሰራዊቱን እያመሰ የሚገኘው ዘረኝነት ችግሩን የበለጠ አወሳስቦት እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል። ዘረኞቹ የሕወሓት ቅጥረኛ የጦር ሹማምንትና መኮንኖች አስፈላጊው ሕግ የሚፈቅደውን ጥቅማ ጥቅም ሳይቀር ለሌላ ብሄር መኮንኖች እና የሰራዊት አባላት በመከልከል ከፍተኛ በድል እያደረሱ እንደሚገኙ በተለያዩ ጊዜያት መዘገቡ አይዘነጋም።

## ጅማ ዉስጥ የወያኔ ፖሊሶች እናትና ልጅ በአሰቃቂ ሁኔታ ገደሉ

ካለፈው አንድ ወር ጀምሮ በአካባቢው የሰፈሩ የፌደራል ፖሊስ አባላት በህዝቡ ላይ የሚወስዱት እርምጃ እየተባባሰ መጥቶ ረቡዕ ሌሊት ለሃሙስ አጥቢያ ፣ ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ የፌደራል ፖሊሶች ወደ አንድ ወጣት መኖሪያ ቤት ሰብረው በመግባት እርሱንና እናቱንበአምስት አምስት ጥይቶች በአሰቃቂ ሁኔታ ገድለው ወደ ካምፓቸው አምርተዋል። የከተማው ህዝብ ተቃውሞውን ለማሰማት ሃሙስ ጠዋት ወደ አደባባይ ቢወጣም የጠበቀው የፖሊስ ዱላ ነው።

እማኞች ለኢሳት እንደገለጹት ወ/ሮ መንበረ የተባሉ የከተማዋ ነዋሪ በሆቴል አገልግሎት ኑሮአቸውን የሚገፉና በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ የሚከበሩ ልጃቸው ዮናስም እንዲሁ በጸባዩ ምስጉን የሆነ የገዢው ፓርቲ ተቃዋሚ ነው። የፌደራል ፖሊሶች ወደ ወ/ሮ መንበረ ሆቴል ገብተው ሲጠጡ ከቆዩ በሁዋላ አንከፍልም በማለት መውጣታቸው ያበሳጨው ልጃቸው ወጣት ዮናስ "የዚህ መንግስት አገልጋዮች ስለሆናችሁ ነው" በሚል ተናግሮአቸዋል። ወታደሮቹ ምንም ሳይሉ ወደ ካምፓቸው ካመሩ በሁዋላ ፣ ሌሊት ላይ መሳሪያቸውን ይዘው በመምጣት የዮናስ እናትን ቤት በር ሰብረው በመግባት ዮናስን በ5 ጥይት ደብድበውታል። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ከቦሌ ለሚ ቤተክርስቲያን ጋር በተያያዘ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ታስረው ለስቃይ እየተዳረጉ ነው

በቦሌ ለሚ በሚባለው አካባቢ የማሪያም ቤተክርስቲያን እንዲፈርስ መደረጉን የተቃወሙ ነዋሪዎች ከፖሊሶች በደረሰባቸው ጥቃት በርካታ ሰዎች የተጎዱ ቢሆንም፣ ፖሊስ ሃይሉን አሰባስቦ በመምጣት በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን ይዞ አስሯል።

አብዛኞቹ ወጣቶች በኮብል ስቶን ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሲሆን፣ ፖሊስ ወደ ድርጅቶቹ በመሄድ ወጣቶችን በጅምላ ማሰሩን የአይን እማኞች ገልጸዋል። ወንድሞቹ የታሰሩት አንድ ነዋሪ ለኢሳት ሲናገር በቦሌ ፖሊስ ጣቢያ ብቻ ከ1 ሺ ያላነሱ ወጣቶች ታስረው ውሃና ምግብ እንዳያገኙ ተከልክለው ሌሊቱን በብርድ አሳልፈዋል። ጧት ውሃ ለማድረስ በሄደበት ጊዜ እጅግ የሚያሳዝን ትእይንት መመልከቱንም ነዋሪው ተናግሯል። ሌሎች ነዋሪዎች ደግሞ ወጣቶቹ በተለያዩ ፖሊስ ጣቢያዎች በመታሰራቸው ቁጥሩን ለማወቅ አስቸጋሪ ነው ይላሉ።

በ7 መኪኖች ተጭነው ወደ አካባቢው የደረሱ የፌደራል ፖሊስ አባላት በወሰዱት እርምጃ ብዙዎች እግራቸው አካባቢ ጉዳት እንደደረሰባቸው ኢሳት በትናንት ዘገባው አሰምቷል። የማሪያም ቤተክርስቲያን ሙሉ በሙሉ እድትፈርስ የተደረገ ሲሆን፣ የቤተክርስቲያኑዋ እቃዎች በመኪና ተጭኖ ተወስዷል።

## የወያኔ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ አለመሳካቱን አመነ

የአምስት አመቱ የዕድገተና ትራንስፎርሜን የተለጠጠ ቢሆንም የማሳካት ሙሉ ኃይል አለን ሲሉ የከረሙት የወያኔ መሪዎች አሁን የዕቅድ ዘመኑ ሊያልቅ ጥቂት ወራት ቢቻ ሲቀረዉ ዕቅዱ በተጠበቀዉ መልክ ሊሳካ እንደማችል ለመጀመሪያ ግዜ አመነ። ዘንድሮ የሚጠናቀቀው የኢህአዴግ የአምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን የተለጠጠ ዕቅድ በግብርና ዘርፍ መዳከም ምክንያት ሳይሳካ መቅረቱን ኢህአዴግ ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ አመነ። ኢህአዴግ "አዲስ ራዕይ" በተሰኘው በርዕዮተ ዓለም ልሳኑ የመስከረም- ጥቅምት 2007 ዓ.ም ዕትም ላይ የአምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የአራት ዓመታት አፈጻጸም አስመልክቶ ባሰፈረው ሐተታ እንደጠቆመው ለጥጦ የያዘውን ዕቅድ ማሳካት እንዳልቻለ በማስቀመጥ አባላትና ደጋፊዎቹን አጽናንቷል።

ግንባሩ ባለፉት አራት ዓመታት በግብርና ፣ በኢንዱስትሪ፣ በአገልግሎት ዘርፎች አመርቂ ውጤት መገኘቱን በደፈናው ካስቀመጠ በኋላ ግንባሩ የተለጠጡ ዕቅዶችን አንግቦ የተነሳና ለማሳካትም ወቅቱ የፈቀደውን ያህል የተንቀሳቀሰ ቢሆንም ከሞላ ጎደል መሠረታዊውን የዕድገት ምጣኔ እንጂ በተለጠጠ አኳሃን የነደፈውን ግብ ማሳካት ሳይችል መቅረቱን አምኗል።

"በራሳችን ተነሳሽነት ለጥጠን ያስቀመጥነው ግብ ላይ ባለመድረሳችን ዛሬም የምንቆጭና ለነገ በእልህና በላቀ ወኔ መነሳሳት እንዳለብን የምንገነዘብ ቢሆንም በአራቱ ዓመታት በርብርብ የተመዘገበው ውጤት የሚያኮራ ነው" ሲል ይጠቅሳል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ጊዜው የሕዝባዊ እምቢተኝነት ነው!!!

በአሁኑ ወቅት በአገራችን በከተሞችና በገጠሮች እየታዩ ያሉ ምልክቶችን በጥንቃቄ የመረመረ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን መታዘቡ አይቀርም።

በአንድ በኩል፣ ወያኔ የተወገደባት፣ ፍትህ የሰፈነባትና የበለፀገች ኢትዮጵያ እውን ሆና የማየት ተስፋችን እየለመለመ ነው። በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ ዉስጥ ለረጂም ዓመታት በሕዝብ ላይ ሰፍኖ የነበረው የፍርሀት ደመና እየገለጠ በመሆኑ ተዘግተው የቆዩ አንደበቶች መናገርና “ይኸ ሁሉ ግፍ ለምን?” ብለው መጠየቅ ጀምረዋል። ይህንን መነቃቃት በአስተሳሰብም፣ በተግባርም፣ በኪነጥበብም እያየነው ነው። የኢትዮጵያ ወጣቶች ለውጥ በአገራችን ሊመጣ እንደሚችል ከማመን አልፎ ራሳቸውን በለውጥ አምጭ ኃይልነት መመልከት ጀምረዋል። በርካታ ወጣቶች ወያኔን በትጥቅ ለመገዳደር የወሰኑ ወገኖቻችንን እየተቀላቀሉ በዚህም ምክንያት ጉልበታቸውን እያፈረጠሙ ነው። የለውጡ እርሾ ከሲቪሉ አልፎ በመከላከያ ሠራዊቱ እና በኢሕአዴግ ድርጅቶች ውስጥም እየተብሰለሰለ ነው። የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት፣ ህወሓት ኢትዮጵያን ለማጥፋት የሚጠቀምበት ኃይል መሆኑ እያበቃ በአንፃሩ የትግሉ አጋር የሚሆንባቸው ሁኔታዎች እየታዩ ነው። በሁሉም የሠራዊቱ ክፍሎች ጉምጉምታው ወደ ጩኸት እየተቀየረ በመሆኑ ሠራዊቱ በአለቆቹ ላይ የሚነሳበት ጊዜ እሩቅ አይደለም። በተለያዩ ምክንያቶች ህወሓትን ወይም ህወሓት የፈጠራቸውን ድርጅቶች የተጠጉ በአጠቃላይ ኢሕአዴግ በሚባለው ስብስብ ውስጥ የሚገኙ ወገኖቻችንም “ለመሆኑ ማንን ነው እያገለገልን ያለነው?” ብለው በመጠየቅ ላይ ናቸው። በዚህም ምክንያት ወያኔ ውስጡ እየተረበሸ ነው። ከኢትዮጵያም ውጭ በሚገኘው ኢትዮጵያዊ ዘንድ ያለው ቁጣና ዝግጁነት ከወትሮው እጅግ የላቀ ነው። በአጭሩ፣ በሁሉም አቅጣጫ፣ ደረጃ በደረጃ የሕዝባዊ እምቢተኝነት እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል።

በአንፃሩ ደግሞ፣ የጨለማ ንጉሥ የሆነው ወያኔ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብን ወደ ፍርሀት ቆፈን ለመመለስ እስሩን ከመቸውም በላይ ያጧጧፈበት ጊዜ ነው። በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በአፋር በሶማሊ … በመላው ኢትዮጵያ ብሩህ ራዕይ የሰነቁ ወጣቶችና አዛውንት ታድነው እየታሰሩ ናቸው። የወያኔ እስር ቤቶች በአርቆ አስተዋይ ዜጎቻችን ተሞልተዋል። ወትሮም ከፍተኛ የነበረው ስደት ብሶበታል፤ ለእውነት በጽናት የቆሙ ጋዜጠኞች ወይ ታስረው፣ አልያም ተሰደው አልቀዋል። የወያኔ የግዴታ ስልጠና አገሩን እያመሰው ነው። የኢትዮጵያዊያን ኑሮ በእጦቶች የታጀበ ሆኗል። የነፃነት እጦት፣ የፍትህ እጦት፣ የመብራት እጦት፣ የስኳር እጦት፣ የዘይት እጦት፣ የታክሲ እጦት፣ የመኖሪያ ቤት እጦት፣ እጦት፣ …. እጦት።

እነዚህ ሁለት ተፃራሪ እውነታዎች ሁለት ተፃራሪ ኃይሎች ለወሳኝ ፍልሚያ ፊት ለፊት መፋጠጣቸዉን በግልጽ ያሳያሉ። ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃነትና ባርነት፣ ፍትህና ጭቆና፣ ደስታና ሀዘን፣ ተስፋና ተስፋ መቁረጥ፣ ብልጽግናና ድህነት፣ እውቀትና ድንቁርና፣ ብርሃንና ጨለማ፣ ለወሳኝ ግጥሚያ ተፋጠዋል። ይህ ፍጥጫ የኢትዮጵያን የወደፊት እጣ ፈንታን በመወሰን ረገድ አቢይ ሚና የሚኖረው ወሳኙ ግጥሚያ - ሕዝባዊ እምቢተኝነት - መጀመሩን አብሳሪ ነው። የነፃነት፣ የፍትህ፣ የተስፋ፣ የብልጽግና፣ የእውቀትና የብርሃን ወገኖች ነን የምንል ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ይህንን ፍልሚያ በድል መወጣት ግዴታችን ነው።

ወያኔ ታጋዮችን ቢያስር ትግሉን አያስርም። በእጦት ኑሮዓችን በማመሰቃቀል በድህነት ሊያንበረክከን ቢሻም፣ በፍጹም አንበረከክለትም። በተዘረፈ የድሆች ድካም ህንፃዎችን ቢገነቡም የራስ ባልሆነ ጌጥ አንኮራም። የወያኔ የሆነ የኛ አይደለም፤ የእነሱ መከበር የኛ መከበር አይደለም። ወያኔ እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ገዢና ተገዢ፤ በዳይና ተበዳይ፣ ገፊና ተገፊ ናቸው።

ተበዳይና ተገፊ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘረኞች፣ ሙሰኞችና ከፋፋዮች የህወሓት ባለሥልጣኖቻቸውና ሎሌዎቻቸው ላይ ይነሳሉ። የተጀመረው ሕዝባዊ እምቢተኝነት አመቺ በሆኑ መንገዶች ሁሉ ይጧጧፋል።

የወያኔ ትዕዛዛትን መሻር፤ በሥራ ላይ መለገም፤ ግብር አለመክፈል፤ አድማ መምታት፤ የወያኔ ካድሬዎችን ማግለልና ማዋረድ፤ የነፃነት ኃይሎችን መደገፍ፤ የፓሊስና የጦር ሠራዊት አባላትን ማቅረብ እና በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ እነሱም የትግሉ አካል እንዲሆኑ ማበረታታት፤ ህሊና ያላቸው የኢሕአዴግ አባላት የሕዝቡን ትግል እንዲያግዙ ማበረታታት … - እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ በርካታ የትግል ስልቶች ከአሁን ጀምሮ በተከታታይ በሥራ ላይ መዋል ይኖርባቸዋል። የወያኔን የጭቆና ምሽግ ከውስጥ መሸርሸር፤ ከውጭ መደርመስ ይኖርበታል። የመሸርሸርና የመደርመስ ሥራዎች ተደጋግፈው እንዲሄዱ ማድረግ ይገባል። ጊዜው የእምቢተኝነት ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የዲሞክራሲና የነፃነት ንቅናቄ የኢትዮጵያ ሕዝብ አጠገቡ ባሉት መሪዎቹ አስተባባሪነት በአንድነት እንዲነሳ ጥሪ ያቀርባል፤ በመላው ዓለም ላይ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረገው ሁለገብ ትግል በጽናት እንዲደግፉ ያሳስባል። ይህንን ትግል በድል መወጣት ግዴታችን ነው፤ እንወጣዋለንም!

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!**

---

## የወያኔ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ አለመሳካቱን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ያለፉት አራት ዓመታት የግብርናው ዘርፍ በአማካይ 7 ነጥብ 15 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት እንዳስመዘገበ የሚጠቅሰው አዲስራዕይ ይህ የዕድገት ምጣኔ በማንኛውም መልኩ ካስቀመጥነው የ14 ነጥብ 9 በመቶ የተለጠጠ ዕድገት ምጣኔ ብቻ ሳይሆን ከመሰረታዊው የ11 በመቶ የእድገት ምጣኔም ትርጉም ባለው ደረጃ ዝቅ ያለ ነው ሲል በይፋ ያምናል።

የግብርና ዘርፉ ከሰባት እስከ ስምንት በመቶ ሲያድግ ኢኮኖሚው ወደ 10 በመቶ ማደጉን፣ የግብርናው ዕድገት ወደ 9 በመቶ ከፍ ሲል ደግሞ ኢኮኖሚው 11 ነጥብ 4 በመቶ ማደጉን አስታውሶ የግብርና ዘርፉ ባቀድነው መሠረት ከ11 እስከ 15 በመቶ ማደግ ቢችል ኖሮ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገቱ ወደተለጠጠው ግብ በተጠጋ ነበር በማለት ያስቀምጣል። የግብርና ዕድገቱ አጠቃላዩን የዕድገት ምጣኔ ዝቅ ወይንም ከፍ የማድረግ ውጤት ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ የሚዋዥቅ ዕድገት የነበረ መሆኑ አጠቃላዩን አገራዊ ፈጣን ዕድገት መጠነኛ መዋዥቅ ያስከተለ ነበር ብሎአል። በአራቱ ዓመታት የግብርና ልማት ዕድገት የተመዘገበው ውጤት በተከታታይ ፈጣን አይደለም ያለው የአዲስራዕይ ዝቅተኛ ዕድገት የተመዘገበበትን 2004 ዓ.ም በአብነት በመውሰድ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ፍጥነታችን ወደታች የወረደ ነበር ሲል ድክመቱን አስቀምጦአል።

መጽሔቱ አያይዞም “በዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ አራት ዓመታት ባለሁለት አሀዝ አማካይ ዕድገት ብናረጋግጥም የተለጠጠውን ግብ ያላሳካንበት ሆነ እድገታችን ወደ 8 ነጥብ 8 በመቶ ዝቅ ያለበትና የመዋዥቅ ገጽታ የተላበሰበት ውጤት የሚያመለክተው የፖለቲካ ጥራታችን በተገቢው ደረጃ ያልተጠበቀባቸው ሒደቶች ውስጥ ማለፋችን ነው ካለ በሁዋላ የልማት ሥራችን በከፍተኛ ፍጥነት የማደግ ውጤት እንዲያስከትል በተሟላ ሕዝባዊ ወገንተኝነት ጠንክረን በላቀ ዲሲፒሊን መንቀሳቀስ ሲገባን በነዚህ መሠረታዊ አቅሞቻችን ላይ መላላት ተፈጥሮ ነበር” በማለት የኢህአዴግን ውስጣዊ ችግር አመልክቷል።

የአምስት አመቱ እቅድ በታቀደበት ወቅት የተለያዩ ምሁራንና በውይይቱ ተሳተፉ የተባሉ ሰዎች እቅዱ ተለጥጧል በሚል መተቸታቸውን በወቅቱ በስልጣን ላይ የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ ተናግረዋልትችቱን አለመቀበላቸውን የገለጹት አቶ መለስ ከተቻለ 15 በመቶ ካልተቻለም 11 በመቶ እድገት ካገኘን ትልቅ ስኬት ነው በማለት የህዝቡንና የምሁራኑን አስተያየት ሳይቀበሉት ቀርተዋል።

ብቸኛው የፓርላማ አባል አቶ ግርማ ሰይፉ እቅዱ በቂ ዝግጅት ያልተደረገበትና ለፖለቲካ ድጋፍ ማስገኛ ተብሎ በስሜት የተዘጋጀ መሆኑን በጽኑ በመተቸት እቅዱ ባይሳካ ጠ/ሚኒስትሩ በሌሎች አገሮች እንደሚታየው ስልጣን ይለቁ ይሆን ሲሉ ጠይቀዋቸዋል አቶ መለስ 11 በመቶ እድገት ቀርቶ 7 በመቶ እድገት ማግኘት ትልቅ ነገር በመሆኑ፣ ኢህአዴግ ስልጣን እንደማይለቅ ምላሽ መስጠታቸው ይታወቃል። ለአቶ መለስ ድጋፋቸውን የገለጹት ሌላው የፓርላማ አባል ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ እቅዱ መሳካትና አለመሳካቱን የዛሬ አምስት አመት እንገናኝና እንየው ሲሉ አቶ ግርማ ሰይፉን ተችተዋልየተለያዩ ምሁራን ኢትዮጵያ ከአለማቀፉ የገንዘብ ተቋም እቅዱን ለመተግበር በቂ የሆነ ገንዘብ ላታገኝ ትችል ይሆናል በማለት ስጋታቸውን በወቅቱ ቢገልጹም አቶ መለስ ስጋቱን አጣጥለውታል አቶ ሃይለማርያም የአምስት አመቱ የልማት ግብ በአብዛኛው ተሳክቷል በማለት በቅርቡ ለፓርላማው ንግግር ማድረጋቸው ይታወሳል።

# የሰንደቅ አላማችን ጠላት ወያኔና ወያኔ ብቻ ነዉ!

ሰንደቅ አላማ ለአንድ አገር ህዝብ የኩራት፤ የአልበገር ባይነት፤ የአንድነትና የታሪክ ተከታታይነት ምልክት ነዉ። ሰንደቅ አላማ በአንድ በኩል የወደፊቱን ብሩህ ተስፋ ክወዲሁ እያሳየን እየዟችሁ የሚለን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በምናብ ወደኋላ እየወሰደን የድልና የመስዋዕትነት ታሪላችንን የሚያስታዉሰን የነጻነት፤ የሠላምና የብሩህ ተስፋ ማህደር ነዉ። የአገራችን የኢትዮጵያ አረንጓዴ፤ ቢጫና ቀይ ሰንደቅ አላማ ትናንትናና ከትናንት ወዲያ በተስፋፊዎች አለመደፈራችንን ብቻ ሳይሆን ዛሬም ዘረኞች የጫኑብንን የመከራ ቀንበር በቆራጥነት ሰብረን ነገና ከነገ ወዲያ የነፃነት አየር እንድንተነፍስ አስረግጦ የሚነግረን የአንድነታችን፤ የተገጋድሏችንና የድላችን ልዩ ምልክት ነዉ። አንድን ኢትዮጵያዊ ሰንደቅ አላማ ላንተ ምንህ ነዉ ብለን ብንጠይቀዉ ጥያቄዉን ዕድሜህ ስንት ነዉ ተብሎ እንደሚጠየቅ አንድና ሁለት ቃል ብቻ ተናግሮ አይመልስም። ሰንደቅ አላማም በአንድና በሁለት ቃላት ምንነቱ የሚገለጽ ተራ ቃል አይደለም። ኢትዮጵያዉያን ተማሩ አልተማሩ፤ ደሃ ሆኑ ኃብታም ፤ወንጀለኛ ሆኑ ወይም ሠላማዊ ለአገራቸዉ ሰንደቅ አላማ የተለየ ቦታ አላቸዉ። ሰዎች የአገራቸዉን ሰንደቅ አላማ የሚወዱትና ለሰንደቅ አላማዉ በክብር መዉለብለብ የህይወት መስዋዕትነት የሚከፍሉት ስለታዘዙ ወይም ስለ ሰንደቅ አላማዉ ተነግሯቸዉ አይደለም። በእርግጥም የሰንደቅ አላማ ክብርና የአገር ፍቅር ለሰዎች ሰንደቅ አላማዉን አክብሩ፤ አገራችሁን አፍቅሩ እየተባለ የሚነገር ነገር አይደለም። አገርንና ወገንን ማክበርና መዉደድ ሰንደቅ አላማን ከማክበርና ከማፍቀር ጋር በቀጥታ የተገናኘ ነዉ።የሰንደቅ አላማ ልዩ ክብርና የአገር ፍቅር ሰዎች ተወልደዉ ከሚያድጉበት ማህበረሰብ፤ ከቤተሰብ፤ከጎረቤትና ከጓደኛ እንደ ምግብና እንደ ዉኃ እየበሉና እየጠጡ የሚያገኙት የሰዉነትና የዜግነት መገለጫ ታላቅ እሴት ነዉ።

ለዚህም ነዉ የማንም አገር ዜጋ አገሩ ዉስጥ ቢኖር ወይም ካገሩ ዉጭ፤ ቢታሰር ባይታሰር፤ ሀብታም ቢሆን ወይም ደሃ፤ የኔ ነዉ የሚለዉን የእናት አገሩን ሰንደቅ አላማ በፍጹም የማይረሳዉ። ከአገራቸዉ ዉጭ የሚኖሩ ሰዎች ደግሞ በተለይም ኢትዮጵያዉያን በተለያዩ ምክንያቶች የሚኖሩባቸዉን አገር ዜግነት ቢወስዱ እንኳን ሰንደቅ አላማቸዉን ባዩና ባስታወሱ ቁጥር የሚሰማቸዉ አገራዊ ስሜት እጅግ በጣም ከፍተኛ ነዉ - እንዲያዉም ከአገራቸዉ ተሰድደዉም ሆነ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከአገራቸዉ ዉጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን ሰንደቅ አላማቸዉን ባዩ ቁጥር የአገራቸዉ፤ የወንዛቸዉ ፤ ተወልደዉ ያደጉበት መንደርና የልጅነት ትዝታቸዉ ባአይናቸዉ ላይ እየመጣ ዕንባ በዕንባ ይተናነቃሉ። ሰንደቅ አላማ ለአንድ አገር ህዝብ አንድ ነገር ነዉ፤ ብዙ ነገር ነዉ፤ ሁሉም ነገር ነዉ። ሰንደቅ አላማ ህዝብን ያስተባብራል፤ ያከባብራል፤ ያዋድዳል፤ መስዋዕትነትን፤ ፍቅርንና ብልፅግናን ያመለክታል።

ዛሬ የሰንደቅ አላማችንን ጉዳይ አቢይ የመወያያ አርዕት አድርገን የወሰድነዉ አለምክንያት አይደለም። በአገር ጥላቻቸዉና በስንደቅ አላማ ንቀታቸዉ የሚታወቁት የወያኔ ዘረኞች "የአብዬን ወደ እምዬ" እንዲሉ ሰንደቅ አላማቸዉ ተዋርዶ ከሚያዩ የቁም ሞታቸዉን የሚመር ትን ዉድ የኢትዮጵያ ልጆች ባንዲራዉን አዋረዱበለዉ መናገራቸዉን ስለማን ነዉ። ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ አገሮች ተስማምተዉ የሚያከብሩት አለም አቀፉ የሰንደቅ አላማ አያያዝ ፕሮቶኮል በአለም አቀፍ መድረኮች ላይ የሁሉም አገሮች ሰንደቅ አላማ በእኩል ደረጃ መቀመጥና መሰቀል አለበት፤ አንድ ላይ መሰቀልና አንድ ላይ መዉረድ አለበት ይላል። ይህንን ፕሮቶኮል ረስቶና ሰንደቅ አላማችንን ንቆ በአለም አቀፍ መድረክ ላይ ከሌሎች አገሮች መሪዎች ጋር የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ እንደ አለባሌ ዕቃ ዘቅዝቆ ይዞ ያዋረደዉ ወያኔዎች "ታላቁ መሪ" ብለዉ የሚጠሩት ነገር ግን የለየለት የአገርና የህዝብ ጠላት የሆነዉ ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ ነዉ። የህወሓትን ባንዲራ በየቦታዉ እየሰቀሉ የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ ተራ ጨርቅ ነዉ ብለዉ የሽቀጥ መጠቅለያ ያደረጉትም መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ ናቸዉ። ዛሬ ደማቅ ሰንደቅ አላማዉን አስመልክቶ በወያኔና በኢትዮጵያ ህዝብ መካከል ያለዉ ትልቅ ልዩነት ትክክለኛዉና ህዝብ የኔ ነዉ ብሎ የተቀበለዉ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ የትኛዉ ነዉ የሚለዉ ጥያቄ ላይ ነዉ እንጂ ባንዲራዉን ማክበር አለማክበር ወይም ማዋረድ ላይ አይደለም።

የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ የእናት አገራችንን የኢትዮጵያንና የህዝቦቿን ታሪካዊ ተከታታይነትና ዘለዓለማዊነት አጉልቶ የሚያሳየን ከሁላችንም በላይ የገዘፈ ግዙፍ አርማ ነዉ፤ ይህ ማለት ደግሞ ሰንደቅ አላማችን ያቻትና ብሎ እንደሚያሳየን አገር አንደ ኢትዮጵያ ሙሉ ህልዉና ያለዉ ህያዉ አካል ነዉ ማለት ነዉ። ሰንደቅ አላማችንን የምንወደዉና የምናከብረዉም ህያዉ አገራችንን የሚወክል ህያዉ አካል በመሆኑ ነዉ። መለስ ዜናዊንና ስብሀት ነጋን የመሳሰሉ በጣት የሚቆጠሩ የትዉልድ ጭንጋፎች ለራሳቸዉ አገር ሰንደቅ አላማ ደንታ ላይኖራቸዉ ይችላል። የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳለ ግን የህልዉናዉና የአንድነቱ መገለጫ የሆነዉን ሰንደቅ አላማ አይንቅም ወይም አያዋርድም፤ አንድ ህዝብ ባንዲራዉን የማይቀበልና የማያከብር ከሆነ ባንዲራዉ አይወክለዉም ማለት ነዉ፡ ኢትዮጵያ ዉስጥ ዛሬ ያለዉ እዉነታም ይሄዉ ነዉ፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ወያኔ ባዕድ አካል የለጠፈበትን ባንዲራ የኔ ነዉ ብሎ አልተቀበለዉም ወይም ባንዲራዉ ይወክለኛል ብሎ አያምንም።

ዘርዓይ ደረስ በ1937 ዓም ሮም ዉስጥ የፋሺስት ጣሊያኖችን ጭንቅላት በገዛ አገራቸዉ እንደ ቅጠል እየጨረገደ ከጣለ በኋላ በጣሊያኖች ጥይት ቆስሎ ሲያዝ የተናገዉ የመጨረሻ ቃል ይህ የጣሊያኖች ባንዲራ ይዉረድና የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ይሰቀል የሚል የጀግንነትና የአገር ፍቅር ቃል ነበር። ጀግናዉ አብዲሳ አጋ በጣሊያን በረሃዎች ጣሊያኖችን እያሳደደ ሲገድል የኢትዮጵያ ባንዲራ ከአጠገቡ አልተለየችም። በቀዳማዊ ኃ/ስላሤና በደርግ ዘመነ መንግስት ተማሪዎች ጧት ወደ ክፍል ከመግባታቸዉ በፊት ተሰልፈዉ የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ በክብር ይሰቅሉ ነበር፤ ማታም ወደ ቤታቸዉ ከመሄዳቸዉ በፊት ጧት በክብር የሰቀሉትን ባንዲራ በክብር አዉርደዉ ነበር ወደየቤታቸዉ የሚሄዱት። ዛሬ የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ ጨርቅ ነዉ ብለዉ የተሳደቡና በዚህ ሰንደቅ አላማ ከገበያ የገዙትን ሸቀጥ እየጠቀለሉ አስራ ሰባት አመት የከረሙ ምናምንቴዎች ናቸዉ በሰንደቅ አላማ ክብርና በአገር ፍቅር ታንጾ ያደገዉን ኢትዮጵያዊ ሰንደቅ አላማዉን አዋረደ እያሉ የአዞ እምባ የሚያነቡት።

ሰንደቅ አላማ በዜጎች ልብ ዉስጥ አንደ እሳት የሚቀጣጠል የአገር፤ የህዝብና የዜግነት መገለጫ የሆነ ታላቅ አርማ ነዉ። ይህ አርማ ደግሞ ከእኛነታችንና ከህልዉናችን ጋር የተጣበቀ አርማ ነዉና መንግስት በተለዋወጠ ቁጥር አይለዋወጥም። ዛሬ ወያኔ የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ አስመልክቶ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር የገባዉ የማይታረቅ ቅራኔም የሚመነጨዉ ከዚሁ ከወያኔ ግራ የተጋባ እዉነታ ነዉ። የዚህ ዘመን ትዉልድም ሆነ ለዚህ ዘመን ትዉልድ አገርና ሰንደቅ አላማ አስረክቦ ያለፈዉ የቀድሞዉ ትዉልድ ሰንደቅ አላማዬ ብሎ የሚጠራዉና ወያኔ የኢትዮጵያ ባንዲራ እያለ የሚጠራዉ ነገር የተለያዩ ናቸዉ።

ባለፉት 75 አመታት አራት ኪሎ ቤ/መንግስትን የተቆጣጠሩት ሦስት ኃይሎች ማለትም የቀኃስ፤ የደርግና የወያኔ አገዛዞች ሁሉም የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ ከራሳቸዉ ጋር ለማያያዝ ሞክረዋል። በንጉሡና በደርግ ዘመነ መንግስት የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ የይሁዳ አንበሳና የወታደራዊዉ መንግስት አርማ ነበረበት፤ ሆኖም እነዚህ ሁለት አርማዎች ያረፉበት የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ በቤተመንግስትና ንጉሡና ፕሬዚዳንቱ በሚጓዙባቸዉ አቶሞቢሎች ላይ እንጂ ሌላ ቦታ አይታዩም ነበር። በመላዉ አገሪቱ በየቀኑ ጧት እየወጣ ማታ ሲመሽ የሚወርደዉና በየግለሰቦች ቤት የሚገኘዉ ሌጣዉ አረንጓዴ፤ ቢጫና ቀዩ ሰንደቅ አላማ ነበር። የኢትዮጵያ ህዝብም ሰንደቅ አላማዬ ነዉ ብሎ የሚያምነዉና የሚቀበለዉ ይህንኑ ምንም አይነት ባዕድ አካላ የሌለበትን አረንጓዴ፤ ቢጫና ቀይ ሰንደቅ አላማ ነዉ።

ወያኔዎች ጫካ ዉስጥ ሆነዉ የትጥቅ ትግል በሚያካሄዱበት ወቅት ያነገቡትና ነጻ አወጣን ባሉበት ቦታ ሁሉ የሰቀሉት የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ ሳይሆን የህወሓትን ባንዲራ ነበር። ከብዙ መረጃዎች እንደተረዳነዉ ወያኔዎች የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ አንደ ተራ ጨርቅ ቆጥረዉ ዕቃ መጠቅለያ አድርገዉት ነበር፤ ይህ ደግሞ የለየለት የጥላቻና የንቀት ምልክት ነዉ።

በአርግጥም ዋና ዋናዎቹ የወያኔ መሪዎች እነ ነመለስ ዜናዊና እነ ስብሐት ነጋ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ህዝብ ይጠሉ ስለነበር ለነሱ ትልቁ ቁም ነገር ህወሐትና የዘረኝነት ምልክት የሆነዉ የህወሓት ባንዲራ ነዉ እንጂ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ አልነበረም። ይህ ፀረ ህዝብና ፀረ አገር ባህሪያቸዉ ደግሞ ጫካ ዉስጥ ብቻ ተወስኖ የቆየ ባህሪ ሳይሆን አዲስ አበባ ገብተዉ ክህዝብ ጋር ሲቀላቀሉም በግልጽ የታየና ምን ግዜም ሊደበቅ የማይችል ባህሪይ ነዉ። የወያኔዉ ቁንጮ መለስ ዜናዊ እኛ ኢትዮጵያዉያን የምናከብዉንና የምንወደዉን ሰንደቅ አላማ "ጨርቅ" ብሎ መጥራቱ አዲስ የጀመረዉ ነገር ሳይሆን ከጫካ ይዞት የመጣዉ የተለመደ አባባል ነዉ። መለስ ዜናዊ ይህንን ጸያፍ ድፍረቱንና ፀረ ሰንደቅ አላማነቱን ለማረሳሳት የባንዲራ ቀን ብሎ ቢያዉጅም የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ልጆቹ፤ አባቶቹ፤ አያቶቹና ቅድም አያቶቹ የተሰዉለት ሰንደቅ አላማ በአለባሌ ሰዉ አንደበት "ጨርቅ" ተብሎ የተጠራበትን ቀን ምን ግዜም አይረሳም።

ከቅርብ ግዜ ወዲህ የወያኔ ዘረኞች ኢትዮጵያዉያንን በተለይም በዉጭ አገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያንን ባንዲራቸዉን አያከብሩም ወይም ባንዲራዉን አዋረዱ እያሉ መክሰስ ጀምረዋል። በነገራችን ላይ ከወያኔዎችና ከጥቂት ሆዳም ተከታዮቻቸዉ ዉጭ የኢትዮጵያ ህዝብ አገር ዉስጥም በዉጭ አገሮችም በሰንደቅ አላማዉ ላይ ያለዉ አቋም ተመሳሳይ ነዉ። ወያኔ ሰንደቅ አላማዉ ላይ ባዕድ አካል ለጥፎ ከዛሬ ጀምሮ ሰንደቅ አላማችሁ ይህ ነዉ ብሎ አዋጅ ሲያወጣ አዋጁን የሰማለት አንድም ሰዉ አልነበረም። እንዲያዉም ህዝብ ሰላማዊ ሰልፍ ሲወጣ፤ ሰርግ ሲደግስ፤ ኳስ ጨዋታ ሲሄድና በተለያዩ ቦታዎች ደስታዉንና ኃዘኑን ሲገልጽ አንግቦ የሚወጣዉ የወያኔን ባንዲራ ሳይሆን አረንጓዴ፤ ቢጫና ቀዩን ሰንደቅ አላማ ነበር። ወያኔ የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ የቀየረዉ በጠመንጃ ሀይል እንደሆነ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት አያያዝ ዙሪያ የአሜሪካ ኮንግረስ ውይይት ተካሄደ

ፋሺስታዊዉ የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚፈጽመዉ ግፍና መከራ የገባቸዉ የአሜሪካ ህግ አዉጪ አካላት አለማቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብቶች የተባለው ድርጅት ለኢሳት በላከው መግለጫ የቶም ላንሶቶስ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ዙሪያ ታዋቂ ሰዎች ሃሳባቸውን እንዲያካፍሉ ጋብዟል። ተናጋሪዎቹ በኢትዮጵያ ያለውን የሰብአዊ መብት አያያዝ በመገምገም የአሜሪካ መንግስት የዲፕሎማቲክና የገንዘብ ድጋፉን ተጠቅሞ በኢትዮጵያ የሚታየው የተበላሸ የሰብአዊ መብት አያያዝ እንዲሻሻል ግፊት ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል ሲል መግለጫው አመልክቷል። ዝግጅቱ አርብ ኖቬምበር 14፣ 2014 ከሰአት 1፡ 30 ፒኤም ላይ ይካሄዳል።

## የዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንቶች ስራቸዉ የሚገመገመዉ ለምርጫው ባላቸዉ ቅርበት ነዉ ተባለ

ትምህርት ሚኒስቴር " የከፍተኛ ትምህርት የኢህአዴግ የምርጫ ድል ልማት ሰራዊት ግንባታ አደረጃጀት ማንዋል፣ ለምርጫ 2007 የተሻሻለ" በሚል ርእስ ያዘጋጀውና ለኢህአዴግ ከፍተኛ ባለስልጣኖች የቀረበው ሰነድ እንደሚለው በአገሪቱ ያሉ ዩኒቨርስቲዎች ፕሬዚዳንቶች ውጤታቸው የሚሞላላቸው በምርጫው ለኢህአዴግ በሚያዘጋጁት የተማሪዎች የድጋፍ ሃይል መጠን ነው።

ሰነዱ የትምህርት ልማት ሰራዊትን በዩኒቨርስቲዎች ለማስፋፋት የተደረገው ስራ ብዙም ውጤት እንዳላስገኘ ጠቅሶ፣ ለዚህም ዋናው ምክንያት በዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ያሉ ከፍተኛ እና መካከለኛ አመራሮች በአደረጃጀቱ ላይ አመኔታ በመጣታቸው ነው ብሎአል። የትምህርት ልማት ሰራዊትን ማደራጀት የፖለቲካ እንጅ የቴክኒክ ጉዳይ ባለመሆኑ ፤ በትምህርት ልማት የሚታቀፉ መሪዎች፣ መምህራን፣ የአስተዳደር ሰራተኞችና ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች የትምህርት ሴክተሩን እቅድ መተግበር ብቻ ሳይሆን፣ በፖለቲካ ስእብናቸው የተገነቡና ኢህአዴግን የሚቀበሉ ተማሪዎች አድርጎ ማውጣት ይጠበቅባቸዋል ሲል ሰነዱ ያመለክታል።

ማንዋሉ የትምህርት ልማት ሰራዊቱ 3 ክንፎች እንዳሉት ይጠቀሳል። ለምርጫ 2007 ዓም የምርጫ አሸናፊነት የሚያዘጋጁ ሁለቱ ክንፎች ማለትም የመንግስትና የህዝብ ክንፎች የሚባሉት ብቻ እንዲዳሰሱ መደረጉን ሰነዱ አመልክቶ፣ የልማት ሰራዊቱ እንቅስቃሴ ከፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ድረስ ተያይዞ ከጫፍ ጫፍ የሚንቀሳቀስ ሃይል እንደሚሆን ገልጿል።

ሰነዱ "በተለይም በአሁኑ ሰአት ፈተና ላይ የጣለን የምርጫ ጉዳይ እንደምናሸንፍ ቃል የተያዘበት ቢሆንም፣ ፈተናዎች የሚፈጠሩት በህዝብ እና በራሱ ታማኝ ባልሆኑ ሃይሎች ማለትም በመንግስት ክንፍ በሚባሉት መምህራን፣ የአስተዳደር ሰራተኞችና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች አይቀለበስም ብሎ ማሰብ ስለማይቻል፣ በዚህም ቀድሞ መዘጋጀት ያለበትና ለሁከት እና ለብጥብጥ መሳሪያ ሊሆን የሚችለው የህዝብ ክንፍ የሚባለው የተማረው ሃይል ሊሆን ስለሚችል ሊታሰብበት ይገባል ብሏል።

ተማሪዎች በኢህአዴግ ላይ ያላቸው አቋም የወረደ መሆኑን ሰነዱ ይገልጻል። በማንኛውም ታቃውሞ ላይ በመገኘት ሰልፍ በማድመቅና ተቃውሞውን ከግብ ለማድረስ ተማሪዎች ሁነኛ መሳሪያ ናቸው የሚለው ሰነዱ፣ በየትኛውም ሀገር እንደታየው አደባባይን የመያዝ ህዝብን አስተባብረው ለተቃውሞ የማሳደም እድላቸው የሰፋ ብቻ ሳይሆን፣ ከዚህም አልፎ የኢህአዴግን የምከታ እርምጃ በመቃወም ለጠላት ጎራ ተሰልፈው የመታጠቅ እድላቸው ከፍተኛ ነው ብለአል።

## ኢህአዴግ በምርጫው ማግስት በዩኒቨርስቲዎች ተቃውሞ እንዳይነሳ የመከላከያ ሰነድ አወጣ

"የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የኢህአዴግ የምርጫ ድል የልማት ሰራዊት ግንባታ አደረጃጀት ማንዋል ለምርጫ 2007" በሚል ርዕስ የተዘጋጀው ሰነድ በጥቅምት ወር በአዋሳ እንዲቀርብ ተብሎ የተዘጋጀ ቢሆንም፣ የሰነዱ ጥራት የወረደና በሰነዱ የተካተቱት ነጥቦች ከልማት ሰራዊቱ ኢህአዴግ ሙሉ በሙሉ መጠቀሙን አያረጋግጥም በሚል በኢህአዴግ ጽ/ቤት በመተቸቱ እንዲሻሻል ከተደረገ በሁዋላ እንደገና ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ.ም የኢህአዴግ አመራሮች እንዲወያዩበት ተደርጓል።

የተዘጋጀው ሰነድ "የኢህአዴግን ምርጫ ውጤታማነት እንዲያመቻች ተብሎ ተሻሽሎ መቅረቡን እንዲሁም የብጥብጥ እና የሁከት መንስኤ የሆነውን ተማሪ በኢህአዴግ አመራር አባላት እየታገዘ መያዝ የሚያስችል " መሆኑ በመግቢያው ላይ ሰፍሯል።

"በምርጫው ሊፈጠር የሚችለውን የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ሁከት እና ብጥብጥ ለማስቀም ተማሪዎችን በማደራጀት መረጃ ለመጥለፍ አመቺነቱ የላቀ እንደሚሆን ታምኖበታል" በማለት የሚያትተው ሰነዱ፣ "የልማት ሰራዊት ግንባታን ወይም የፖለቲካ ሰራዊት ግንባታ በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተደራጀና በተቀናጀ ሁኔታ በማቀጣጠልና በማስቀጠል ተቋማዊ ለዉጡን እውን በማድረግ የትምህርት ጥራትና አግባብነትን ፤ ምርጫ 2007 ትንም ውጤታማ ለማድረግ እና የኢህአዴግን አሸናፊነት ለማረጋገጥ" እንደሚያግዝ ይገልጻል።

"የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ልማት ሠራዊት ግንባታ ምንነት፤ አስፈላጊነትና ፋይዳ" በሚለው ርዕስ ስር ደግሞ "ተማሪዎች በኢህአዴግ ላይ ያላቸው አቋም የወረደ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በማንኛውም የተቃውሞ ድምፅ ከተጠሩ ሰልፍ የሚያደምቁ፣ ተቃውሞን ከግብ ለማድረስ ሁነኛ መሳሪያ ናቸው።" ሲል ይፈርጃቸዋል። በማያያዝም "ተማሪዎች በየትኛውም ሐገር እንደታየው አደባባይን የመያዝ፣ ህዝብን አስተባብረው በተቃውሞ የማሳደም እድላቸው የሰፋ በመሆኑ፣ ከዚህም ሲያልፍ ፤ የኢህአዴግ ምከታን በመቃወም ለጠላት ጎራ ተሰልፈው የመታጠቅ እድላቸው ከፍተኛ ነው" ሲል ይገልጻቸዋል።

ስለዚህም ይላል ትምህርት ሚኒስቴር ያዘጋጀው ሰነድ የከፍተኛ ትምህርት የልማት ሰራዊት በማደራጀትና በመገንባት ማስማራት የግድ ይላል። ሰነዱ አክሎም "በተለይም በዚህ ሰዓት የምርጫ ፈተና ላይ የጣለን የምርጫ ጉዳይ፣ እንደምናሸንፍ ቃል የተያዘበት ቢሆንም፤ ፈተናዎች የሚፈጠሩት በህዝብ እና በራሱ ታማኝ ባልሆኑ ሃይሎች ማለትም በመንግስት ክንፍ በመሆኑ የኢህአዴግ አይሸነፍም የሚለው ቃል አይቀለበስም ብሎ ማሰብ አይቻልም።" ሲል የኢህአዴግን ፍርሃትና ጥርጣሬ ያመላክታል። የከፍተኛ ተቋም ተማሪዎች "የአመፅ እና የብጥብጥ መነሻ ሊሆን የሚችሉ ሃይሎች መሆናቸውን በአክራሪዎች ሲጠለፉ፤ ከመንግስት ይልቅ ሃይማኖታቸውን እየመረጡ በባህርዳር ዩኒቨርስቲ፤ በጅማ ዩኒቨርስቲ ፤ በመቀሌ ዩኒቨርስቲ እና በሌሎችም የትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን ትተው ሲኮበልሉ ተመልክተናል ብሎአል።

"እስካሁን በዩኒቨርስቲዎች ከተተገበሩት የልማት ሰራዊት እንቅስቃሴ የምንረዳው የከፍተኛ የትምህርት ተቋም አንድን ምዕራፍ በአግባቡ ሳያከናውን ወደሚቀጥለው የግንባታ ምዕራፍ ቢሸጋገር የትምህርት ልማት ሠራዊቱ በተሟላ ሁኔታ ወይም የተሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ ሊወጣ የሚችል ሰራዊት ተገንብቷል ማለት አለመቻሉን በመሆኑ ሁሉም የሰራዊቱ ክንፎች በሙሉ በምርጫው ዙሪያ በቂ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ፣ ተገቢውን አደረጃጀትና አሰራር ዘርግቶ ለመካከለኛው አመራር፣ ለዝቅተኛ አመራር፣ ለመምህራን፣ ለምርምር አካላት፣ ለድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችና ተማሪዎች ግልጽ ስምሪት መስጠት፣ ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ እያንዳንዱን የሰራዊት ክንፍ ወደሚፈለግበት የጥንካሬ ደረጃ እየደረሰ መሆኑንና የተቋሙ እቅድ በውጤታማነት መፈጸሙን ማረጋገጥ አለበት" ሲል ሰነዱ መመሪያ ያስተላልፋል።

ዴሞክራሲያዊ ግንኙነት የሚመሰረተው በኢህዴግ መሪ ድርጅትነት ብቻ ነው የሚለው ሰነዱ ቀጣዩ ስኬት በኢህአዴግ መሪ ድርጅት ቀጣይነት ላይ የተመሰረተ ነው ብሎአል። በመንግስት እና በከፍተኛ ተቋማት በሚገነቡ የሰራዊት ክንፎች መካከል ስለሚኖረው አሰራርና አደረጃጀት ቀጣይ መመሪያ እየተዘጋጀ መሆኑን ከኢህአዴግ ምንጮች ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

## ጅማ ዉስጥ የወያኔ ፖሊሶች እናትና ልጅ በአሰቃቂ ሁኔታ . . .

( ከገጽ 1 የዞረ )

እናቱ ወ/ሮ መንበረ "እባካችሁ ልጄን አትገድሉብኝ" ሲሉዋቸው ፖሊሶቹ እርሳቸውንም በ5 ጥይቶች ገድለዋቸው ወደ ካምፓቸው ተመልሰዋል። ድርጊቱ ያስቆጣቸው የከተማዋ ነዋሪዎች ከቀብር በፊት የተቃውሞ ሰልፍ ቢያደርጉም፣ በፖሊሶች ዱላ ተደብድበው ተበታትነዋል። ጅማ ጢት አካባቢ በተኩስ ስትናወጥ መዋሉዋንም ነዋሪዎች ተናግረዋል። በጉዳዩ ዙሪያ አንድ የጅማ ነዋሪ አነጋግረናል።

ከአንድ ሳምንት በፊት አንዋር የተባለ ወጣት በጩቤ በአሰቃቂ ሁኔታ ከተገደለ በኋላ ህዝብ ድርጊቱን ለመቃወም ወደ አደባባይ ቢወጣም በተመሳሳይ መልኩ በፖሊሶች ተደብድቦ ተባርሯል። ከአንድ ወር በፊት ደግሞ ኬኔዲ መንገሻ የሚባል አዲስ ቅጥር የመንግስት ሰራተኛ በፖሊሶች ተገድሏል። በአካባቢው የሰፈረው የፌደራል ፖሊስ በህዝቡ ላይ የሚወሰደው እርምጃ መጨመሩ ህዝቡ በስጋት እንዲኖር አድርጎታል። ነዋሪዎች እንደሚሉት ሁኔታው ከአቅማቸው በላይ እየሆነ ነው።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## እንግሊዝ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌን በተመለከተ ደብዳቤ መጻፏን ወያኔ አረጋገጠ

የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ዴቪድ ካሜሮን አቶ አንዳርጋቸው ፅጌን በተመለከተ ለወያኔዉ ጠቅላይ ሚኒስትር ደብዳቤ መጻፋቸውንና ወያኔም አቋሙን ግልጽ ማድረጓን የወያኔዉ ኮሙዩኒኬሽን ጽሕፈት ቤት ሚኒስትሩ አቶ ሬድዋን ሁሴን ተናገረ። ሬድዋን በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ባለፈዉ ማክሰኞ በሰጠዉ ጋዜጣዊ መግለጫ፣ ዴቪድ ካሜሩን ለጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደብዳቤ መጻፋቸውን የተለያዩ የውጭ ሚዲያዎች መዘገባቸውን ሰምቻለሁ ካለ በኋለ "ለምን ጻፉ ማለት አይቻልም፤ ጥያቄዉ መሆን ያለበት ምን መለሳችሁ ነው፤" በማለት የተለመደ የማጭበርበሪያ ቃላት ደርድሯል።

የተለያዩ የእንግሊዝ ሚዲያዎች ኢትዮጵያ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ላይ ቀደም ሲል የተፈረደውን የሞት ቅጣት እንዳትተገብር እንዲሁም ኢትዮጵያ ለሚገኘው የእንግሊዝ ኤምባሲ አቶ አንዳርጋቸውን የመጐብኘት ቋሚ ፈቃድ እንዲሰጥ በደብዳቤያቸው መጠየቃቸውንም ሬድዋን ሁሴን ተናግሯል።

ለዴቪድ ካሜሮን ደብዳቤ መልስ መስጠቱን ያረጋገጠዉ ሬድዋን፣ "በተጨባጭ የተፈረደበትን ግለሰብ ነው የያዝነው፤ እንዲህ ብታደርጉት ባታደርጉት ብሎ ማንሳት ይቻላል። ምክንያቱም እነሱም የሚመለከታቸው በመሆኑ። በዚህ ምክንያት ግን የእኛ መልስ በራሳችን ሕግ መሠረት ዓለም አቀፍ ሕጉም በሚለው መሠረት የምናደርገውን እናደርጋለን፤" ብሏል። ኢትዮጵያ የምትተገብረው የራሷን ሕግ መሆኑን የገለጹት አቶ ሬድዋን፣ "ከነጭም ከጥቁርም የሚመጣን ደብዳቤ ተንተርሰን ምንም አንተገብርም፤" ብሏል። ከዚህ በተጨማሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዴቪድ ካሜሮን ደብዳቤ ጽፈው፣ በኢትዮጵያ በኩልም መልስ ተሰጥቷል ያለዉ ሬድዋን ሁሴን በደብዳቤው የቀረቡ ጥያቄዎች ቅሬታ እንዳላስነሱ ሁሉ መልሱም ቅሬታ አያስነሳም የሚል ተስፋ በኢትዮጵያ በኩል መኖሩን ተናግረዋል።

"እነሱ ዜጋዬ ነው ብለዋል፤ የእነሱ ዜጋ እንደ ቼ ጉቬራ ነፃ አውጣ ተብሎ ኢትዮጵያ ውስጥ አልተላከም። የእነሱ ዜጋ ከነበረ የእንግሊዝን ዴሞክራሲ ይበልጥ ለመጨመር መታገል ይችል ነበር። ነገር ግን በኢትዮጵያ በቅጥር ነብሰ ገዳይነት ካልተሰማራ በስተቀር ሌላ ሚና አልነበረውም፤" ብለዋል።

## ከ40 በላይ በምእራብ አርማጭሆ ተወላጆችና ታጣቂዎች

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የተፈጸሙ የብዙዎችን የግፍ ግድያ ጨምሮ በዜማ ያዘጋጃቸውን ቀስቃሽ ዘፈኖቹን ለገበያ እንዳይቀርብ በወያኔ ደህንነቶች አማካኝነት እንደተከለከለ ምንጮቻችን አመልክተዋል። ባሻ ጥጋቡ የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ለሱዳን በሰጠው ሰፊ የድንበር መሬትን በተመለከተ ተቃውሞ በማሰማታቸውና ለድርጊቱ ፊርማቸውን ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በአገዛዙ እንዲገደሉ መደረጋቸው በስፋት መዘገቡ አይዘነጋም።

በተያያዘ ዜና በታች አርማጭሆ ሽመሊጋራ ወረዳ ትጥቅን ለማስፈታት እየተነቀሳቀሱ የሚገኙት የአካባቢው ቅጥረኛ ሚሊሻዎችንና ፓሊሶች ከነዋሪዎች ጋር ከፍተኛ ግጭት ውስጥ መግባታቸው ታውቋል። በግጭቱ በተፈጠረው የተኩስ ልውውጥ እስካሁን ከ 3 በላይ የአገዛዙ ቅጥረኞች መገደላቸውን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በነዋሪዎች በኩል 1 ግለሰብ መገደሉን እንዲሁም በርካቶች የመቁሰል አደጋ እንደደረሰባቸው ተመልክቷል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ መሪነት በወረዳዋ የተጀመረው ትጥቅ የማስፈታት ዘመቻ በከፍተኛ ሁኔታ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ይነገር እንጂ የታች አርማጭሆ ነዋሪዎች እና ገበሬዎች በጋራ በመቆም መሳሪያ አናስረክብ በማለት እምቢተኝነታቸውን አጠናክሩው በመቀጠላቸው በአካባቢው ከፍተኛ ውጥረሰት ነግሶ አሁን ድረስ መቀጠሉን ለማወቅ ተችሏል። በአካባቢው የተከሰተው የሕዝብ እምቢተኝነትና ቁጣ ያስደነገጣቸው የአካባቢው የወያኔ ቅጥረኞች በከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ እንደሚገኙም ለማወቅ ችለናል።

በፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ የተቀነባበረውን አገር የማጥፋት ሴራና በሕዝቦች ላይ እያደረሰ ባለው መጠነ ሰፊ በደል በመቆጨት አገዛዙን በትጥቅ ትግል ለማስወገድ ከሚታገሉ የነፃነት ሃይሎች ጋር ለመቀላቀል በርሃ እየከተቱ የሚገኙ ወጣቶች፤ ጎልማሶች እንዲሁም በአገዛዙ ስር ተቀጥረው ይሰሩ የነበሩ የፓሊስ፤ የመከላከያ ሰራዊትና የአካባቢ ሚኒሻዎች ቁጥር ከዕለት ወደ ዕለት እየተበራከተ መምጣቱን እየተከታተልን መዘገባችን አይዘነጋም። ከሰሞኑ በጋምቤላ ክልል በጨፍጫፊውና ፋሽስታዊው አገዛዝ የተማረሩ ቁጥራቸው ከ 50 በላይ የሆኑ የልዩ ሃይል ወታደሮች ከነ ሙሉ ትጥቃቸው አገዛዙን ከድተው በአካባቢው የሚንቀሳቀሱ የነፃነት ሃይሎችን መቀላቀላል መቻላቸው መዘገቡ ይታወሳል።

## የሰንደቅ አላማችን ጠላት ወያኔና ወያኔ ብቻ ነዉ!

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ሁሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን የማይወደዉንና በሀይል የተጫነበትን ባንዲራ ተቀብሎ እንዲኖር ያደረገዉም በጠመንጃ ሀይል ነዉ።

ለመሆኑ እነሱ እራሳቸዉ የለየላቸዉ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ጠላት የሆኑት የወያኔ መሪዎች በዉጭ አገሮች የሚኖሩና አክርረዉ የሚቃወሟቸዉን የኢትዮጵያ ልጆች ባንዲራዉን አዋረዱ እያሉ ተደጋጋሚ ክስ የሚያሰሙት ለምንድነዉ? አንዳንድ ከህልዉናቸዉ ይልቅ ለማይጠረቃዉ ሆዳቸዉ ያደሩ ደካማ ግለሰቦችስ ይህንን የወያኔ መሠረተ ቢስ ክስ እየሰሙ አንደ ገደል ማሚቶ ደግመዉ ደጋግመዉ የሚያስተጋቡት ለምንድነዉ? አገራችን ኢትዮጵያ ሁለት የተለያዩ ባንዲራዎች ሊኖራት እንደማይችል ሁላችንም እናዉቃለን። ለመሆኑ ይህ እኛ ሰንደቅ አላማ እነሱ ባንዲራ እያልን የምንጠራዉ ነገር አንድና ተመሳሳይ ነዉ? ወያኔና በየቦታዉ ያስቀመጣቸዉ የገደል ማሚቶዎች ከሁሉም ነገር አስቀድመዉ መመለስ ያለባቸዉ ይህንን ጥያቄ ነዉ። እኛ ኢትዮጵያዉያን ከህጻንነታችን ጀምሮ የኛ ነዉ እያልን ያሳደገንን፤ የመራንን፤ አቅጣጫ ያሳየንነና በተለይ በልጅነታችን ት/ቤት እያለን ጧት በክብር ሰቅለን ማታ ላይ በክብር እያወርድን በክብር እናስቀምጥ የነበረዉን አረንጓዴ፤ ቢጫና ቀይ ሰንደቅ አላማችንን ማክበርና መዉደድ ብቻ ሳይሆን ለዚህ ሰንደቅ አላማ ዘለዓለማዊነት አንድ ህይወታችንን እንሰጣለን። ሰንደቅ አላማዉን የማያከብር ህዝብ የለም፤ እኛም ኢትዮጵያዉያን ሰንደቅ አላማችንን እንወዳለን፤ እናከብራለንም፤ የምንወደዉና የምናከብረዉ ሰንደቅ አላማ ግን ባዕድ አካል የተለጠፈበትን የወያኔን ባንዲራ ሳይሆን የነፃነታችን፤ የአንድነታችን፤ የሰላማችንና የመዋዕትነታችን ምልክት የሆነዉን አረንጓዴ፤ ቢጫና ቀዩን ሰንደቅ አላማ ነዉ። ይህንን ሰንደቅ አላማ ደግሞ እኛ ኢትዮጵያዉያን ብቻ ሳንሆን ይህንን የጥቁር ህዝብ የነጻነትና የመስዋዕትነት ታሪክ ምልክት የሆነ ደማቅ ሰንደቅ አላማ አያሌ አፍሪካዉያንም ያከብሩታል። ለምሳሌ የስምንት የአፍሪካ አገሮች ባንዲራ አቀማመጡ ይለያያል አንጂ ቀለሙ አረንጓዴ፤ ቢጫና ቀይ ነዉ፤ ከዚህ በተጨማሪ የሌሎች 23 አፍሪካ አገሮች ባንዲራ ደግሞ ቀዩና አረንጓዴዉ ቀለም አለበት። ይህ ሁሉ የሚያሳየን ሰንደቅ አላማችን የፓን አፍሪካ ባንዲራ እየተባለ በተለያዩ የአፍሪካ አገሮችም የሚከበርና የብዙ አፍሪካ አገሮች ሰንደቅ አላማ መሰረት መሆኑን ነዉ።

የወያኔ ዘረኞች ኢትዮጵያ ዉስጥ የነበሩትንና በዉጭ አገሮች የሚገኙ አማራጭ የመረጃ ምንጮች ሁሉ ጥርቅም አድርገዉ ዘግተዉ እንደቤት ዉስጥ ዕቃቸዉ በሚቆጣጠሩት ቴሌቪዥን፤ ሬዲዮና ጋዜጣ "በሬ ወለደ" አይነት ዉሸታቸዉን ጧትና ማታ በተደጋጋሚ አየተናገሩ ለግዜዉም ቢሆን ህዝብን ማደናገር ይችሉ ይሆናል። ሰንደቅ አላማዉን የሚወደዉንና የሚያከብረዉን ኢትዮጵያዊም እነሱን ስለተቃወመ ብቻ ባንዲራዉን አዋረደ እያሉ ህዝብን ሊያታልሉ አንዳንድ ወደ ገባዎችንና ጥቂት የዋሆችን ሊያሳምኑ ይችሉ ይሆናል። ሆኖም የኢትዮጵያን ህዝብ እንወዳለን ፤ ለኢትዮጵያ አንድነት እንቆማለን፤ የዚህ አንድነት ምልክት የሆነዉን ሰንደቅ አላማም እናከብራለን አያሉ ታቦት ተሸክመዉ ቢምሉም የሚያምናቸዉ ቀርቶ ከጉዳይ ቆጥሮ የሚሰማቸዉ አንድም ዜጋ የለም። የወያኔ ዘረኞችና ቡችሎቻቸዉ የሚባቸዉ ቢሆን ኖሮ ዉስጣችን ያለዉን ከፍተኛ የአገር፤ የወገን፤ የባንዲራና የሉዓላዊነት ስሜት ደግመን ደጋግመን እንነግራቸዉ ነበር፡ ሀኖም እነሱን ከማስወገድ ጀምሮ አገራችንን እስከማረጋጋት ድረስ ብዙ አስቸኳይ የሆነ አገራዊ አደራና አገራዊ ስራ ይጠብቀናልና ለዛሬዉ እዚህ ላይ እናብቃ።

**የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ያሸንፋል!**